# "የኢትዮጵያ ልጆች" እና "የእስራኤል ልጆች"

ነቢየ እግዚአብሔር አሞጽ፡ "'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።"

ማለትም፡ "ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" ሲል፡ የተናገረው ቃል፡ ለዚህ ሓተታ፡ መርሕ ኾኖ ተጠቅሶ ቀርቧል።

በዚህ ቃል መሠረት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ማለትም፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ እውነተኞቹ፡ የኢትዮጵያ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ ጥንት፡ ከአዳምና ከሔዋን ጀምረው፡ እስከዛሬም ቢኾን፡ እንደፈጣሪያቸው ፈቃድ፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ፡ ሲያካኺዱት ለኖሩት፡ የአምልኮ ሥርዓታቸው፡ ፈጽመው ምልክት እንደሌላቸው፡ አረጋግጠን እንናገራለን።

የቅዱሱ ኪዳን አካላት ለኾኑት፡ ለሰባቱ ቃል ኪዳናት፡ የተለያዩ ምልክቶች ቢኖሯቸውም እንኳ፡ በእነዚሁ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ኹሉም፡ ምንጊዜም፡ ተጠብቀው ሲፈጸሙ የኖሩትና ወደፊትም የሚኖሩት፡ እውነተኛውንና የመንፈስ ቅዱስን አምልኮ በተከተለ መልኩና ይዘቱ፡ ነው። ይህም ማለት፡ ምልክቶቹ ኹሉ፡ በረቂቁ የመንፈስ ቅዱስ ጣቶች፡ በረቂቁ መንፈሳዊ ልቦናቸው ጽላት ላይ ተጽፈው፡ በሕያውነት የሚፈጸሙ እንጂ፡ በግዙፉ በድን ጽላት ወይም፡ ሰሌዳ ላይ ተቀርጸው በሚታዩበትና በሚነበቡበት፥ በሚዳሰሱበትና በሚጨበጡበት ቍሳዊ አካልነታቸው መልክና ይዘት፡ የአምልኮው ሥርዓት የሚፈጸምባቸው አይደሉም ማለት ነው።

በተለይ ለእስራኤል ልጆች ብቻ ተለይተው በተሰጧቸውና ገዝፈው በሚገኙት፡ በኋለኞቹ፡ በሦስቱ ቃል ኪዳናት ምልክቶች አማካይነት የሚፈጸመው፡ ይኼኛው ዓይነት የአምልኮ ሥርዓት፡ ተፈላጊነት ኖሮት የሚካኼደው፡ በራሳቸው፡ "ዕብራውያን፥ አይሁድ፥ እስራኤል" ተብለው መጠራትን ለሚወድዱት፥ ዛሬም ድረስ፡ የአብርሃም፥ የይስሓቅና የያዕቆብ ልጆች በመኾናቸው በሚመኩት ዘንድ እንጂ፡"**ሳያዩ ያመኑበትን ሃይማኖት ይዘው በመገኘታቸው፡ መለኮታዊው አንደበት፡ 'ብፁዓን ናቸው!' ብሎ፡ ለባለሟልነት ሞገስ የሚያበቃውን የክብር ማዕርግ አጐናጽፎ ለተናገረላቸው፡ የቅድስቲቱ የኢትዮጵያ ልጆች ለኾኑት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት አለመኾኑ፡** ሊታወቅ ይገባል።

ይህንም እውነታ፡ በተጻፈ ቃል የሚያምነው ዓለም፡ ራሱ በተቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግበው ከሚገኙት፡ ማስረጃዎች መካከል፡ ለጊዜው፡ ከዚህ ከተነሣንበት ርእስ ጋር፡ "አግባብነት አላቸው!" የሚባሉትን፡ ከዚህ እንደሚከተሉትን፡ ሦስቱን ያህል ብቻ ጠቅሰን በማቅረብ፡ እናረጋግጣልን።

## የአብርሃምን የግርዛት ቃል ኪዳን በሚመለከት።

፩ኛ፡ በእግዚአብሔር አማኝነቱና ካህንነቱ፥ የእውነትና የሰላም ንጉሥም በመኾኑ፡ የእግዚአብሔር ልጅና የማርያም ልጅ ለኾነው፡ ለዘለዓለማዊው ካህን ንጉሥ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳሚ አርአያ፥ ለኢትዮጵያዊነትም አብነት የኾነው፥ በአጼነት የማዕርግ ስሙ፡ "መልከ ጼዴቅ" የተባለው ኢትዮጲስ፡ ከአዳምና ሔዋን፡ በኖኅና በቀደሙት ቅዱሳንና ቅዱሳት አያት ቅድማያቶቹ አማካይነት ተላልፎ በደረሰው ሥርዓት መሠረት፡ የአምልኮ መሥዋዕትንና ቍርባንን ያቀርብ የነበረው፡ በኅብስትና ጽዋ ብቻ እንደነበረ፡ በግልጽ የታወቀ እውነት ነው።

አብራም፡ ቀድሞ፡ በጣዖት አምልኮ ቀንበር ሥር ይዳክር በነበረበት ጊዜ፡ ለእርሱና ለወገኖቹ፡ ዲያብሎስ ያስለመዳቸው፡ የባዕድ አምልኮው አፈጻጸም፡ ይካኼድ የነበረው፡ በደመ ነፍስ የተፈጠሩትን የእንስሳትንና የአዕዋፋትን ብቻ ሳይኾን፡ የሰዎችንም ደም በማፍሰስ ጭምር መኾኑ፡ በጽሑፍ ተመዝግቦ ይታወቃል።

ይኸው አብራም፡ በዚያ፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ መምህርነትና ካህንነት፡ ወደእግዚአብሔር የአምልኮ ሥርዓት እንዲገባ በኾነ ጊዜ፥ ለግርዛቱም ቃል ኪዳን በቅቶ፡ ስሙ፡ ወደ"አብርሃም"ነት በተለወጠ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ ከእርሱና የእርሱ ከኾኑት ልጆቹ ጋር የተካየደውን ቃል ኪዳን ያጸናው፡ ከራሱ አካል በሚፈስስ ደም ያደረገው፡ ያለ ምክንያት እንዳልነበረ፡ መገንዘቡ፡ አግባብ ይኾናል።

"ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም!" በተባለው የመጽሓፍ ቃል መሠረት፡ ዲያብሎስ፡ በሰዎች ላይ ያሸከመውን፡ የጣዖት አምልኮቱን ቀንበር ለማጽናት፡ ደምን በማፍሰስ አጠናክሮ ያሠረውና ያተመው በመኾኑ፡ ያን የኃጢአት ቀንበር ለማስወገድና ያን መከረኛ ሰብአዊ ፍጡር፡ ከዚያ እሥራቱ ፈትቶ፡ ነጻ ለማውጣት፡ የሌላ እንስሳ ደም ሳይኾን፡ የራሱ፡ "የአብርሃም ልጅ ነኝ!" የሚለው፡ የዚያ ሰብአዊ ፍጡር ደም፡ በግርዛት ጊዜ፡ ደሙ እንዲፈስስ አስፈላጊና ተገቢ ኾነ፤ "የኃጢአት ሥርየት ተገኘ!" የሚያስሰኘው፡ ይህ ነው። (ዕብ. ፱፥ ፳፪።)

ለዚህ ነው እኮ፡ "የአብርሃም ልጆች ነን!" የሚሉት፡ አይሁድ፡ ይህ ልማድ አልለቃቸው ብሎ፡ ከግብፅ ከወጡ በኋላና ጽላተ ኪዳኑን በደብረ ሲና ከተቀበሉ በኋላም እንኳ፡ ወደዚያው የጣዖት አምልኳቸው እየተመለሱ የቀጠሉት። በዚህም ብቻ ሳይወሰኑ፡ በመጨረሻ፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ደም፡ እንደፋሲካ በግ፡ በመስቀል ላይ እንዲፈስስ በማድረግ፡ የዚያን፡ የለመዱትን፡ የጣዖቱን የመሥዋዕት ደም ጥማታቸውን ለማርካትና ሥጋውንም በመብላት፡ ከስስት ረሃባቸው ለመጥገብ፡ ከጲላጦስ ጋር፡ ያን ያህል አጠንክረውና አብዝተው የተጯጯኹት። ፍላጎታቸው ሲፈጸምም፡ እንዲያ የተደሰቱትና የፈነደቁት፡ ከዚህ የተነሣ መኾኑ፡ እዚህ ላይ ሊታወስ ይገባል። ይህ ኹሉ ኹኔታ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ በፈጸሙት ግፍና ጭካኔ፥ እስከዛሬም ባላቸው ጥላቻና ቅዋሜ፡ እውንና እርግጥ ኾኖ፡ ይኸው ይታያል።

የእስራኤል ልጆች፡ የሃይማኖታቸው ክህደትና የምግባራቸው ዓመፅ ባስከተለው፡ የክፋትና የኃጢአት ጠንቅ ምክንያት፡ በመካከሉ፡ እንዲህ፡ ደም በማፍሰስ፡ መልከ ጼዴቃዊዉን የኅብስትና ጽዋ ሥርዓት፡ ተክቶ የነበረውን፡ ይህንኑ፡ የኦሪቱን ግዳጅም እንኳ ቢኾን፡ ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም የተወለደው፡ ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ አስወግዶ፡ ያንኑ፡ ደገኛውን፡ የሥጋ ወደሙን የመሥዋዕትና የቍርባን ሥርዓት፡ ወደዚያው፡ ወደቀደመውና ወደጥንቱ፡ መልከ ጼዴቃዊው፡ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት የኅብስትና ጽዋ ሥርዓት መልሶታል።

እንደዚሁ፡ እንደመሥዋዕቱ የሥርየት ደም ኹሉ፡ በዘሮቹ፡ በአይሁድ ላይ ጸንቶ እንዲፈጸም የተደረገው፡ የአብርሃሙ ዓይነት ሥጋዊ ግርዛት፡ ከመጀመሪያውም፡ ለኢትዮጵያ ልጆች አላስፈለጋቸውም። ምክንያቱም፡ በእነርሱ ዘንድ የነበረው ግርዛት፡ መንፈሳዊውና እውነተኛው የኾነው፡ የልቦና ግርዛት እንጂ፡ "የእስራኤል ልጆች ነን!" የሚሉት አይሁድ የሚያካኺዱት፡ በሰውነት አካል የአባለ ዘር ብልት ላይ የሚደረገው፡ ግዙፉ፡ የሥጋ ግርዛት ስላልነበረ ነው።

ስለዚህ፡ ግርዛትን ያመጡት፡ የኢትዮጵያ ልጆች ሳይኾኑ፡ አብርሃምና ዘሮቹ፡ ቀደም ብሎ ከነበረው፡ የአምልኮ ሓረጋቸው ግንድ ተስቦ፡ እንዲህ፡ ሲያያዝ በመጣው ጠንቀኛ ልማዳቸው ምክንያት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል። የእስራኤል ልጆች፡ ያንኑም፡ የግዝረትን የቃል ኪዳን ሥርዓት መጠበቅ እንኳ ተስኗቸው፡ በአምልኳቸው፡ እግዚአብሔርን ማስቀየማቸውን መቀጠላቸው፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ዜና መዋዕል፡ በሰፊው የተተረከ ጉዳይ ነው።

በአንድ በኩል፡ በሃይማኖቱና በምግባሩ፡ ፈጣሪውንና አምላኩን፡ እግዚአብሔርን፡ ያስደሰተው አብርሃም ግን፡ ሣራ ከሞተች በኋላ፡ "አቤሜሌክ" የተባለው የአጼው፣ ወይም፡ የመልከ ጼዴቅ ወገን የኾነችውን ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን በማግባቱና ከእርሷ ልጆችን በመውለዱ፡ ቀድሞ፡ በታላቁ መልከ ጼዴቅ የተቀበለውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱን፡ በበለጠ ሊያጸናው ችሏል።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ አይሁድ የተዉትንና ያበላሹትን፡ የግርዛቱን የቃል ኪዳን ሥርዓት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚሁ፡ በአብርሃም ኢትዮጵያዊነት፡ እግዚአብሔር በሚቀበለው፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፡ ከሃይማኖቱና ከምግባሩ ጋር፡ በትክክለኛውና በአግባቡ መልክና ይዘት፡ እየፈጸሙት በመኖራቸው፡ እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች ለመኾን በቅተዋል። እውነተኞቹ የእስራኤል ልጆች መኾናቸውንም አረጋግጠዋል።

## የሙሴን፡ ጽላተ ሕግ ቃል ኪዳን በሚመለከት።

፩ኛ፡ እግዚአብሔር፡ በሙሴ እጅ የገለጣት፡ "ታቦተ ጽዮን"፥ ወይም፡ "ታቦተ ሕግ"፥ ወይም፡ "የምስክር ታቦት" የምትባለው፡ ጽላተ ኪዳን፡ የተሰጠችው፡ ለእስራኤል ልጆች እንጂ፡ ለኢትዮጵያ ልጆች እንዳይደለ፡ በጊዜው የኾነው፡ የዜና መዋዕሉ ድርጊት፡ በሚበቃ ያስረዳል። ለእነርሱ ተለይታ የተሰጠቻቸውም፡ ከላይ ከተወሳው፡ ከዘር ሲያያዝ ከመጣው፡ የጣዖት አምልኮ ፍቅራቸውና ዝንባሌአቸው ጠንቅ የተነሣ፡ በአባቶቻቸው አምላክ፡ በእግዚአብሔር ላይ በፈጸሙት፡ የሃይማኖት ክህደትና የአምልኮ ዓመፅ ምክንያት እንደኾነ፡ የኢትዮጵያ ልጆች ቀርተው፡ በራሳቸው፡ በእስራኤል ልጆችና "ሃይማኖታዊ ነኝ!" በሚለው፡ በፍጥረተ-ዓለሙ ዘንድ ጭምር፡ በገሃድ የሚታወቅ እውነታ ነው።

በእስራኤል ልጆች ዘንድ፡ ያን የመሰለው፡ አሳፋሪና አሳዛኝ ኹኔታ የታየው፥ የአባቶቻቸው፡ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ ለእነዚሁ ታማኞቹ ግለሰቦች፡ የገባውን ቃል ኪዳን በማሰብ፡ በታላቅ ክንዱና ኃይሉ በላከው በሙሴ አማካይነት፡ የማይታበለውን የተስፋ ቃሉን እንደፈጸመላቸው፡ አርባ ቀን እንኳ ሳይቆይ፡ ወዲያው እንደነበረም፡ በዜና መዋዕሉ፡ በግልጽ ተነግሯል። ጽላተ ኪዳኗ፡ ለእነርሱ እንድትሰጥ ምክንያት የኾነው፡ ያ፡ አሳፋሪውና አሳዛኙ ኹኔታ የተከሠተው፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ከዚያ አሠቃቂ ኑሮአቸው፡ ሊታደጋቸው፡ ወደእነርሱ የላከው ሙሴ፡ ማን መኾኑን፡ እነዚሁ፡ የእስራኤል ልጆች፡ የኾነውን ነገር ኹሉ፡ ደኅና አድርገው ካወቁ በኋላ ነው። እርሱ ሙሴም፡ ያን የመሰለውን ትድግና ሊያመጣላቸው የቻለው፡ በምን ዓይነቱ መለኮታዊ ኃይል መኾኑን፡ እየራሳቸው፡ በነፍስ ወከፍ፡ ኹሉንም ድርጊት፡ በእየራሳቸው ላይ እየደረሰ ባዩትና ሊመሰክሩ በሚችሉበት አቋም ኾነው፡ በሙሉ ከተረዱ በኋላ ነው።

አዎን! ሙሴ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር ተምሮና አውቆ፡ ይህንኑ ምንነትና ማንነት፡ በሃይማኖት ከተቀበለ በኋላ፥ ይኸው ምሁሩ ካህንም፡ ኢትዮጵያዊት ልጁን ሲጳራን ድሮለት፡ ከእርሷ፡ ኹለት ልጆችን ካፈራ በኋላ፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ፡ የእስራኤልን ልጆች፡ ከግብፅ የ፬፻ ዓመታት የባርነት ቀምበር ነጻ ያወጣቸው ዘንድ፡ እግዚአብሔር እንደላከው፡ በሚገባ ያውቃሉ።

ያ አሳፋሪና አሳዛኝ ኹኔታ፡ በአንድ ወገን፡ የእነርሱን የውለታቢስነት ግብር የሚያጋልጥ ሲኾን፡ በሌላ በኩል ደግሞ፡ እንኳንስ ባሕርዩ የኾነውን፡ የእግዚአብሔርን ርኅራኄና መሓሪነት ቀርቶ፡ ሰብአዊ ፍጡር የኾነውን፡ የሙሴን ደግነትና ጻድቅነት፡ ማለትም፡ እውነተኛነት ብቻ ሳይኾን፥ ከፈጣሪው የተፈቀደለትን፡ የአማላጅነቱ ሥልጣንና ጸጋ፡ የቱን ያህል እንደሠራ፡ አረጋግጦ አሳይቷል።

ይህም፡ "ወነበበ እግዚአብሔር ለሙሴ፤ ወይቤሎ፦ 'ሑር! ወአፍጥን ወሪደ፡ እምዝየ፣ እስመ አበሱ ሕዝብከ፡ ዘአውጻእከ እምድረ ግብፅ። ወወጽኡ እምፍኖት፡ ዘአዘዝክዎሙ፤ ወገብሩ ላሕመ፤ ወሰገዱ፤ ወሦዑ ሎቱ፤ ወይቤሉ፡ 'እሉ እሙንቱ፡ አማልክቲከ፡ እስራኤል! ዘአውጽኡከ እምድረ ግብፅ!' ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ፡ 'ርኢኩ ዘንተ ሕዝበ፤ ወናሁ፡ ዝንቱ ሕዝብ፡ ግዙፈ ክሣድ። ወይእዜኒ ኅድገኒ፤ እጥፍኦሙ በመዓትየ፤ ወእሠይመከ ላዕለ ሕዝብ ክቡድ ወዓቢይ።'

*"ወሰአለ ሙሴ ቅድመ አምላኩ፤ ወይቤ፡- 'ለምንት እግዚኦ! መዓት ትትመዓዕ፡ ላዕለ ሕዝብከ፣ ዘጸውአከ እምድረ ግብፅ፣ በኃይል ጽኑዕ፤ ወበመዝራዕት ልዑል፥ ወዓቢይ፣ ከመ ኢይብሉ ግብፅ፡ 'በእኩይ አውጽአሙ፡ ከመ ይቅትሎሙ በውስተ አድባር፤ ወከመ ያጥፍአሙ እምድር፤' አቅርር መዓተከ፡ ዘተማዕከ! ወመሐሬ ኩን፡ ላዕለ እከዮሙ ለሕዝብከ። ተዘከር፡ አብርሃምሃ፥ ወይስሓቅሃ፥ ወያዕቆብሃ አግብርቲከ፣ ዘመሓልከ ሎሙ በርእስከ፤ ወትቤሎሙ፡- ‹ብዙኀ አበዝኆ ለዘርእክሙ፡ ከመ ከዋክብተ ሰማይ ብዙኀ፤ ወኵሎ ዘንተ እሁብ ለዘርእክሙ፤ ወይመልክዋ ለዓለም።›'"*

*"ወሠረየ እግዚአብሔር፡ በእንተ እኪት፡ ዘይቤ ይግበር ላዕለ ሕዝብ።"*

*ማለትም፡ "እግዚአብሔርም ሙሴን፡ እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- 'ከግብፅ አገር ያወጣሃቸው ወገኖችህ ኃጢአት ሠርተዋልና፡ ከዚህ ፈጥነህ ተነሥተህ ውረድና፡ ወደእነርሱ ኺድ! እኔ ካዘዝኋቸው ሥርዓት ወጥተው፡ በደሉ፤ የላሙንም ምስል ሠርተውና ከፊታቸው አቁመው ሰገዱለት፤ መሥዋዕቱንም ሠዉለት፤ ‹እስራኤል! ከግብፅ አገር ያወጡህ አማልክቶችህም፡ እኒህ ናቸው!› አሉ።' እግዚአብሔር፡ ሙሴን፡ 'ይህን ሕዝብ አየሁት፤ እነሆም፡ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው። አኹንም፡ በቍጣዬ አጠፋቸው ዘንድ ተወኝ! አንተንም፡ ከዚህ በሚበልጥና በሚበዛ ወገን ላይ እሾምሃለሁ!' አለው።*

*"ሙሴም፡ በፈጣሪው ፊት ቆሞ፡ እንዲህ ሲል፡ የልመና ጸሎትን አቀረበ፡- 'አቤቱ! በጽኑ ኃይል፥ ከኹሉ በላይና ታላቅ በኾነም ሥልጣን፡ ከግብፅ አገር ያወጣሃቸውን ሕዝብህን፡ ለምን ተቈጥተህ ታጠፋቸዋለህ? ግብፃውያንስ፡ 'በተራራው ሊገድላቸው፥ ከዚህ ዓለምም ሊያጠፋቸው፡ እስራኤልን፡ ለክፉ ነገር አወጣቸው!' እንዳይሉ፡ በእነርሱ ላይ የተቀጣጠለውን ቍጣህን፡ እባክህ አብርድ! በክፋታቸውም ላይ፡ ሕዝብህን ይቅር የምትል ኹን! ‹ለዘለዓለሙ ሊወርሷትና ሊገዟት፡ ዘራችሁን፡ እንደብዙዎቹ የሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ፤ ይህንም ኹሉ፡ ለልጆቻችሁ እሰጣቸዋለሁ!› ብለህ፡ በራስህ የማልክላቸውን፡ አገልጋዮችህን፡ አብርሃምን፥ ይስሓቅንና ያዕቆብን አስብ!'"*

*"እግዚአብሔርም፡ 'በሕዝቡ ላይ አደርገዋለሁ!' ያለውን የቍጣውን ቅጣት፡ 'ይቅር!' ብሎ ተወው።"*

እግዚአብሔር አምላክ፡ በሙሴ አንደበትና እጅ፡ ያን ኹሉ፡ ድንቅና አስፈሪ ተአምራት ያደረገው፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች፡ የእርሱን ሃይማኖታዊ ማንነትና የተአምራቱን ምግባራዊ ምንነት እያሳያቸው፥ እርሱም፡ ከእነርሱ የሚፈልገው የአምልኮ መሥዋዕት፡ በምን መልክና ይዘት ሊቀርብለት እንደሚገባ ሊያስተምራቸው፥ ያም፡ እርሱ በሚፈቅደውና በሚወድደው፡ በእውነትና በመንፈስ ሊኾን እንደሚገባ ሊያሳያቸው እንደነበረ፡ ለማንም አስተዋይ ሃይማኖታዊ ተመልካች፡ ግልጽ እንጂ፡ ሥውር ሊኾን፡ ከቶ አይችልም።

ራሱ ሙሴ፡ ዐብሯቸው በነበረባቸው አርባ ዓመታት ውስጥ፡ እንዲህ፡ እርሱን ከመቃወምና እግዚአብሔርን ከማሳዘን በቀር፡ አንዳችም መልካም የሃይማኖትና የምግባር፥ የአምልኮም ፍሬ ሳያሳዩት የኖሩ መኾናቸው ተጽፏል። ይህ ብቻ አይደለም፤ ወደምድረ ከነዓን ከገቡበት ጊዜ ጀምሮም፡ በዚያ አሳፋሪና አሳዛኝ ኹኔታ፡ ለእስራኤል ልጆች የተሰጠችው፡ ይህችው ጽላተ ኪዳን፡ በእነርሱ እጅ በቆየችባቸው ዘመናት ኹሉ፡ ወደጥንቱ ጣዖታዊ ባዕድ አምልኳቸው እየተመለሱ፡ ይፈጽሙት በነበረው የክህደትና የዓመፅ፥ የክፋትና የኃጢአት ግብራቸው ምክንያት፡ ፈጣሪያቸውን ከማሳዘን በቀር፡ ለእነርሱም ኾነ ለሚተካቸው ትውልድ፡ የሚበጅ፡ አንዳችም መልካም የኾነ፡ የሃይማኖትና የምግባር የአምልኮ ፍሬ ሊገኝባቸው እንዳልተቻለ ተዘክሯል።

ስለዚህ፡ ከተቀመጠችበት ሣጥኗ የተነሣ፡ "ታቦተ ጽዮን" ተብላ የምትጠራውን፡ ይህችን የጽላተ ሙሴ ቃል ኪዳን፡ እግዚአብሔር፡ እንደግዝረቱ ቃል ኪዳን ኹሉ፡ ከነምልክቷና ኹለንተናዋ ጋር፡ ወደምድረ ኢትዮጵያና ወደኢትዮጵያ ልጆች እንድትመለስ አደረገ።

እዚህ ላይ፡ ሊወሳ የሚገባ፡ አንድ እውነታ አለ፤ ይኸውም፡ እንደግዝረቱ ኹሉ፡ ይህችም ጽላት፡ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ ምንጊዜም ያላስፈለገቻቸው፥ የማታስፈጋቸውም መኾኗ ነው፤ ምክንያቱም፡ በእነዚያ፡ ኹለት የዕብነ በረድ ጽላት (ሰሌዳዎች) ላይ፡ በእግዚአብሔር ጣቶች የተቀረጹት አሥሩ ቃላት፡ በኢትዮጵያ ልጆች ልቦና ላይ፡ በተፈጥሮ እና በመንፈስ ቅዱስ ተጽፈውና ሕያዋን ኾነው፡ ኢትዮጵያዊዉንም ሰውነታቸውን፡ ጽላትና ታቦት፥ መንበርና መቅደስ አድርገውት፡ ህልውናቸውን፡ በእግዚአብሔር ሕይወት እንዲቀጥል ስላስቻሉት ነው።

ይህም፡ የእስራኤል ልጆች፡ በአብርሃም ምክንያት፡ የግርዛቱን ቃል ኪዳን፥ በሙሴም ምክንያት፡ የታቦተ ጽዮንን ቃል ኪዳን ለመቀበል ከመጠራታቸው፡ ከበርካታ ሺሆች ዓመታት በፊት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ለእውነተኛውና ለገነታዊው ሕይወት በቅተው፡ እየኖሩት ነበር ማለት ነው። ያም ሕይወት፡ ያች ጽላተ ኪዳን፡ ለእስራኤል ልጆች ልታስገኝላቸው ትችል የነበረው ሲኾን፡ እነርሱ፡ የእስራኤል ልጆች ግን፡ ለእግዚአብሔር የገቡትን ቃል ኪዳን፡ ባለመታደል፡ ጠብቀው ሊፈጽሙት ስላልቻሉ፡ ያን የመሰለው መልካም ሕይወት፡ ለዘለዓለም ቀረባቸው።

## የዳዊትን የዙፋን ቃል ኪዳን በሚመለከት።

፫ኛውና ዋናው፡ የሓተታችን መነሻ የኾነውን፡ ኪዳነ ዳዊትን ስንመለከት፡ ተመሳሳይ ኹኔታዎችን እናገኛለን። ይኸውም፡ ለእስራኤል ልጆች ተሰጥተው፥ ነገር ግን፡ እነርሱ፡ ለእነዚያ፡ ለቀደሙት፡ ኹለት ቃል ኪዳናት፡ ባለቤትነት ቀርቶ፡ ለባለአደራነቱም እንኳ፡ ሊበቁ ባለመቻላቸው፡ እነዚያ ስጦታዎች፡ ለኢትዮጵያ ልጆች እንደተዳረጉ ኹሉ፡ አኹንም፡ ለዚህኛው ቃል ኪዳን፡ እኒሁ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ተቀባዮችና ባለአደራዎች ብቻ ሳይኾኑ፡ ባለቤቶች ጭምር መኾናቸው ነው።

ይህንም እውነታ፡ እግዚአብሔር፡ ለዳዊት በሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት፡ "የዳዊት ልጅ!" ተብሎ፥ በመልከ ጼዴቅ የቃል ኪዳን ሥርዓት መሠረት ደግሞ፡ "ካህኑ ንጉሥ" ተብሎ፡ በዘለዓለማዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት ዙፋን ላይ የተቀመጠው፡ የእግዚአብሔር ልጅና የኢትዮጵያዊቷ የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!" ማለትም፡ "ከይሁዳ ነገድ የተገኘው አንበሳ ድል አደረገ!" በሚለው፡ መለኮታዊ ቃል፡ በኢትዮጵያ ልጆች ላይ፡ በአዋጅ ነግሦ መኖሩ፡ ተጨባጭ ምስክር ኾኖ፡ እሙንነቱን ያረጋግጠዋል።

የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ምግባሩ ያላቸው፡ እኒህ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ለዚህ፡ ፍጹም ጣፋጭ ለኾነው፡ ዘለዓለማዊ ፍሬ፡ እየራሳቸውን ለማብቃት ይችሉ ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በመለኮታዊ ጥበቡ የተጠቀመበትን ድንቅ ኹኔታ፡ እስኪ እንመልከት!

በቀዳሚነት፡ እግዚአብሔር፡ በዲያብሎስ የጣዖት አምልኮ የጠፋውን የአሕዛብን ዓለም ለማዳን፡ በኢትዮጵያዊው መልከ ጼዴቅ አማካይነት፡ አብርሃምን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማንነቱና ምንነቱ፥ ከዚያም ለግርዛት ቃል ኪዳኑ አብቅቶ እንደተጠቀመበት ኹሉ፥

በመካከሉ ደግሞ፡ የእርሱ ዘሮች የኾኑት፡ የእስራኤል ልጆች፡ በጣዖታውያኑ ግብፃውያን የአምልኮ ግዞትና የባርነት አገዛዝ ሥር ከሚማቅቁበት ቀንበር፡ ነጻ አውጥቶ ሊያድናቸው በወሰነ ጊዜ፡ በኢትዮጵያዊው ካህን ዮቶር አማካይነት፡ ሙሴን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማንነቱና ምንነቱ፥ ከዚያም ለጽላቱ ቃል ኪዳን አብቅቶ እንደተጠቀመበት ኹሉ፥

በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ እነዚህኑ፡ እስካኹን የተጠቀሱትን፡ ሦስቱንም ቃል ኪዳኖች ከማፈራረሳቸው የተነሣ፡ **"ግዙፈ ክሣድ፥ትውልድ ዕሉት፥ ወዓማፂት፥ ወዘማዊት!"** ማለትም፡ **"አንገተ ደንዳና፥ ከሃዲ፥ ዓመፀኛና አመንዝራ ትውልድ!"** ወደተባሉት፥

በተለይም፡ "ውስተ ፍኖተ አሕዛብ፡ ኢትሑሩ! ወሀገረ ሳምር፡ ኢትባኡ! ወሑሩ ባሕቱ፡ ኀበ አባግዕ ዘተሓጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል።" ማለትም፡ "ወደአሕዛብ መንገድ አትኺዱ! ወደሳምራውያን አገርም፡ አትግቡ! ነገር ግን፡ ከእስራኤል ወገን ወደጠፉት በጎች ኺዱ!"

ቀጥሎም፡ "ኢትፈነውኩ፡ ዘእንበለ ኀበ አባግዕ፡ ዘተሓጕላ፡ ዘቤተ እስራኤል!" ማለትም፡ "ከእስራኤል ወገን ወደኾኑ፡ ወደጠፉት በጎች ብቻ እንጂ፡ ወደሌላ አልተላክሁም።" በሚል ቍርጥ ቃል፡ እነዚህኑ፡ ፈጽመው የጠፉትን፡ የእስራኤል ልጆች ለማዳን፡ ራሱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ከርስቶስ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ በፍጹም ኢትዮጵያዊነት ተወልዶ፡ በዚህ፡ መለኮታዊ ማንነቱና ኢትዮጵያዊ ምንነቱ፡ ታላቁን ተልእኮውን ፈጸመ። (ማቴ. ፲፥ ፭-፯፤ ፲፭፥ ፲፭፥ ፳፬።)

ከላይ፡ የአብርሃምን ግዝረትና የሙሴን ጽላተ ኪዳን በሚመለከት እንደታተተው፡ ለኢትዮጵያ ልጆች፡ የ"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ማኅተማዊ ምልክትም አላስፈልጋቸውም። ምክንያቱም፡ "እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፤ ወገብረ መድኀኒተ በማእከለ ምድር፤ አንተ አጽናዕካ፡ ለባሕር፡ በኃይልከ። አንተ ሰበርከ፡ ርእሰ ከይሲ በውስተ ማይ፤ ወአንተ ቀጥቀጥከ፡ አርእስቲሁ ለከይሲ፤ ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ ኢትዮጵያ።"

ማለትም፡ "እግዚአብሔርማ፡ ዓለም ሳይፈጠር ጀምሮ ባለው መንግሥቱ፡ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መካከል፡ መድኃኒትን አደረገ፤ አንተ፡ በኃይልህ፡ ባሕርን አጸናሃት፤ አንተ፡ የእባቡን ራስ፡ በውኃ ውስጥ ሰበርህ፤ የእባቡን ራሶች ቀጠቀጥህ፤ ለኢትዮጵያም ሕዝብ፡ ምግባቸውን ሰጠሃቸው።" ከሚለው የነቢዩ ቃል የተነሣ፡ እግዚአብሔር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሰው ከመኾኑም በፊት ኾነ፡ ሰው ከኾነም በኋላ፡ ምንጊዜም፥ ለዘለዓለምም፡ ንጉሣቸው ስለኾነ ነው።

በዚህ መሠረት፡ ኢትዮጵያና ልጆቿ (ሕዝቧ)፡ እግዚአብሔር፡ እርሱ፡ ራሱ፡ ንጉሣቸው ኾኖ፥ ቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያምም፡ ንግሥታቸው ኾና፡ በመንፈስ ቅዱስ መራጭነትና ሿሚነት፡ ወንዶቹ፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር፥ አጼ"፥ ሴቶቹም፡ "ሥይምተ እግዚአብሔር፥ አጼዪት" እየተባሉ፡ የወንድ ኾነ፡ የሴት እንደራሴዎቻቸውን፥ እንዲሁም፡ ለቤተ ሕዝቡ፥ ለቤተ ክህነቱና ለቤተ ምልክናው የእልቅና ሹመትና አገልግሎት የሚኾኑትን፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን፡ በቤተ ሕዝቡ የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ፡ መርጠውና አስመርጠው እየመደቡላቸው በሚያገለግሉባት፡ በእግዚአብሔርዋ የኢትዮጵያ መንግሥት ሲተዳደሩ ኖረዋል።

እግዚአብሔር፡ ከአሕዛብ መካከል ያገኛቸውን፥ እንደብርቅ የሚያያቸውንና የሚጨነቅላቸውን፡ የእስራኤልን ልጆች፡ አጥብቆ ለመያዝ፡ በሰብአዊው የግርዛት ደም እየታተመ የቀጠለው፡ የአብርሃም ቃል ኪዳንና የራሱ፡ የእግዚአብሔር ቃል ማደሪያ የኾነችው የጽላተ ሙሴ የቃል ኪዳን ታቦት አልበቁትም። ሌላ ሦስተኛ ቃል ኪዳን አስፈለገው። ያንንም፡ መንፈስ ቅዱስ ገና አስቀድሞ፡ በብሉዩ ዘመን፡ የአብርሃም የልጅ ልጅና የልጁ የይስሓቅ ልጅ በኾነው፡ በያዕቆብ ላይ ዐድሮ፡ እንዲህ ሲል፡ ባናገረው ትንቢት ገልጾታል፡-

"ይሁዳ! ይሴብሑከ አኀዊከ፤ እደዊከ፡ ላዕለ ዘባኖሙ፡ ለጸላእትከ፤ ይሰግዱ ለከ፡ ደቂቀ አቡከ። ይሁዳ! እኁለ አንበሳ! እምኀዝአትከ ዕርግ ወልድየ! ሰከብከ፣ ወኖምከ፣ ከመ አንበሳ፤ ወከመ እኁለ አንበሳ፡ አልቦ ዘያነቅሓከ። ኢይጠፍእ ምልክና፡ እምይሁዳ፤ ወምስፍና፡ እምአባሉ፣ እስከ አመ ይረክብ፡ ዘጽኑሕ ሎቱ፤ ወውእቱ፡ ተስፋሆሙ፡ ለአሕዛብ።"

ማለትም፡ "ይሁዳ! ወንድሞችህ ያመሰግኑሃል፤ እጆችህ፡ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ናቸው፤ የአባትህ ልጆችም፡ ለአንተ ይሰግዱልሃል። ይሁዳ! አንተ፡ የአንበሳ ግልገል! ከመደብህ፡ ተነሥ! ውጣ! ልጄ! እንደአንበሳ ተኛህ፤ አንቀላፋህም፤ እንደአንበሳ ደቦል፡ ሊቀሰቅስህ የሚችል የለም። ለአሕዛብ፡ ተስፋቸው የኾነውና እርሱ የሚጠበቀው እስኪመጣ ድረስ፡ በትረ መንግሥት፡ ከይሁዳ፥ የግዛት ሥልጣንም፡ ከወገኑ አይጠፋም።" (ዘፍጥ. ፵፱፥ ፰-፲።)

ኋላም፡ በሓዲሱ ዘመን፡ በወንጌላዊዉና በባለራእዩ ዮሓንስ ላይ ዐድሮ፡- "ወይቤለኒ፡ አሓዱ፡ እምውስተ እልክቱ ሊቃናት፡- 'ኢትብኪ! ናሁ፡ ሞአ አንበሳ! ዘእምነገደ ይሁዳ፤ ዘእምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፤ ከመ ይፍትሓ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፤ ወለማኅተሚሃ።"

ማለትም፡ "ከእነዚያ አለቆች፡ አንዱ፡ እንዲህ አለኝ፡- 'አታልቅስ! ይህችን መጽሓፍ፡ ይገልጥ ዘንድ፥ ማኅተሚኗንም፡ ይከፍት ዘንድ፡ እነሆ! ከዳዊት ሥር፥ ከይሁዳ ወገን የኾነ አንበሳ ድል አደረገ!" ብሎ ትንቢቱን ተርጕሞታል። (ራእ. ፭፥ ፭።)

ለዚህ፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!" ለሚለው፡ ለቃል ኪዳኑ፡ የዛፍ ፍሬ፡ ዘሩና ሥሩ፡ ከላይ የተጠቀሰው የብሉዩ የትንቢት ቃል ቢኾንም፡ ዐብሮት የተያያዘውና ከእርሱ የሠረፀው፡ "መሓለ እግዚአብሔር ለዳዊት፡ በጽድቅ፤ ወኢይኔስሕ፤ 'እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ!'"

ማለትም፡ "እግዚአብሔር፡- 'ከወገብህ ከሚወጣው ዘርህ የሚወለደውን ልጅህን፡ በዘለዓለም መንግሥት ዙፋንህ ላይ አስቀምጠዋለሁ!' ሲል፡ ለዳዊት፡ በእውነት በገባው ቃል ኪዳን፡ ምንጊዜም አይጸጸትም።" የሚለው መለኮታዊው የተስፋ ቃል ደግሞ፡ መሠረቱና ግንዱ መኾኑ፡ የታወቀና የታመነበት እውነታ ነው። (መዝ. ፻፴፩፥ ፲፩። ፪ሳሙ. ፯፥ ፲፪-፲፬።)

ይህ አምላካዊ ተስፋ፡ በቃል ኪዳን የተሰጠው፡ ለእስራኤሉ ልጆች ንጉሥ፡ ለዳዊት እንጂ፡ ከኢትዮጵያ ልጆች፡ ለአንዱ አልነበረም። ይኹን እንጂ፡ እንደአብርሃሙ የግርዛት ቃል ኪዳንና እንደሙሴዋ ጽላተ ኪዳን ኹሉ፡ እነሆ፡ በፍጻሜው ዘመን፡ እኒሁ፡ የእስራኤል ልጆች፡ በእግዚአብሔር ላይ ሲፈጽሙት በኖረው፡ በተለመደው ክህደታቸውና ዓመፃቸው፥ ክፋታቸውና የአምልኮ አመንዝራነታቸው ምክንያት፡ ለዚህኛውም፡ እግዚአብሔር፡ በመደምደሚያው፡ ለዳዊት ለሰጠው፡ ለቃል ኪዳኑ ዘር፡ ለባለቤትነት ቀርቶ፡ ለባለደራነትም እንኳ የማይበቁ ኾነው ተገኙ።

ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ ከላይ በተጠቀሱት፡ በኹለቱ ቃል ኪዳናት ላይ፡ በየመልኩ ለደረሰው ፈታኝ ኹኔታ፡ መፍትሔ የሚኾነውን መንገድ፡ ከኢትዮጵያ ልጆች በኩል ሊያገኝ እንደቻለ ኹሉ፡ አኹንም፡ ለዚህኛው ቃል ኪዳኑ፡ ህልውና መቀጠል የበቃች፡ አንዲት ንጽሕት የኾነች ድንግል ሰውነት፡ ከኢትዮጵያ ልጆች መካከል፡ ራሷን አቅርባለት ተገኘች። እርሷም፡ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ ናት።

ይህች፡ ስመ ጥሩና ገናና ንግሥት፡ በእግዚአብሔር ፈቃድና ዝግጅት፡ የባለቃል ኪዳኑ ንጉሥ፡ የዳዊት ልጅ፡ ሰሎሞንና የቃለ እግዚአብሔር መገኛ የኾነችው፡ ታቦተ ጽዮን ወደሚገኙባት፡ ወደኢየሩሳሌም ኼዳ፡ የዳዊት ልጅ የተባለውን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችውን፡ ድንግል ማርያምን ያስገኘውን፡ የዳዊትን የቃል ኪዳን ዘር ብቻ ሳይኾን፡ ታቦተ ጽዮንን፡ ከታማኞች ጠባቂዎቿና አገልጋዮቿ ጋር፥ እንዲሁም፡ ከእስራኤል ልጆች መካከል፡ የግዝረቱ ቃል ኪዳን፡ እውነተኞች ፈጻሚዎች የኾኑትን ምርጦች ጭምር፡ ወደኢትዮጵያና ወደኢትዮጵያ ልጆች አመጣች።

## ኋለኞቹን፡ የእስራኤል ልጆች ሦስት ቃል ኪዳናት በሚመለከት።

እግዚአብሔር፡ እነዚህን ሦስት ቃል ኪዳናት፡ ለምን፡ በተለይ፡ ለእስራኤል ልጆች ብቻ ሰጠ፤ መስጠት ብቻ ሳይኾን፡ ለምን፡ እስከመጨረሻ ድረስ እንዲጸኑላቸው፡ ራሱ፡ በኢትዮጵያዊነት ሰውነት እስከመወለድ፥ ከዚያም፡ በመስቀል መከራ፡ እስከመሠቃየት፥ ሥጋው ተከታትፎና ተተልትሎ፥ ደሙም፡ እንደጐርፍ ፈስሶ፥ እስከሞትና ወደመቃብር እስከመውረድ የሚያደርስ መሥዋዕትነትን መክፈል፡ ለምን አስፈለገው?

ይህ ኹሉ የኾነው፡ ያለበቂና ያለጽኑ ምክንያት አይደለም። እግዚአብሔር፡ በኖኅ ዘመን እንደነበረውና እንደዛሬው ኹሉ፡ የዲያብሎስ የኾነውን፡ ክፋትንና ሓሰትን እንጂ፡ እርሱን፡ እግዚአብሔርንና የእርሱ የኾኑትን፡ እውነቱን፥ መንግሥቱንም የሚፈልግ፡ አንድም ሰው፡ በታጣበት፡ እጅግ አሳዛኝና አሠቃቂ ጊዜ ላይ ደርሶ ይገኝ ነበር። ያም ጊዜ፡ የአሕዛቡ ዓለም፡ በዲያብሎስና በሠራዊቱ ቊጥጥርና አመራር ሥር፡ የፌጥኝ ተይዞ፡ ፈጽሞ፡ በጣዖት አምልኮ የተዋጠበት ነበር። በዚያን ጊዜ የነበረው፡ ያ ኹኔታም፡ ከመጀመሪያው አንሥተው፡ የእርሱ፡ የእግዚአብሔር፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቹ የኾኑትን፡ ጥቂቶቹን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት አያጠቃልልም ነበር።

በዚያን ጊዜና ኹኔታ ውስጥ፡ እግዚአብሔር፡ አብርሃምን የመሰለ፡ አንድ፡ ፍጹም ታማኝ ሰውን አገኘ። እርሱንም ካገኘ በኋላ፥ ማንነቱንና ምንነቱንም በፈተና ካረጋገጠ በኋላ፡ በቃው። እርሱን ምክንያት አድርጎ፡ አረማዊዉን ዓለም፡ ከዲያብሎስ የገዢነት ቀንበር አላቅቆ፡ ወደእርሱ እውነትና እውቀት፥ ሕይወትና መንግሥት ማርኮ ለመውሰድ፡ ማናቸውንም ዋጋ ከመክፈል በቀር፡ ዘሩን ሳይቀር፡ እንግዴህ ወዲህ፡ በምንም፥ በምንም ምክንያት ሊተወው፥ ለጥንታዊው ባላጋራም፡ መልሶና አሳልፎ፡ ላይሰጠው ወሰነ፡ እግዚአብሔር።

የቅዱሱ ኪዳን አካላውያት አባላት ከኾኑት ከሰባቱ ቃል ኪዳናት መካከል፡ ቀዳሚዎቹና መሠረቶቹ፡ ሦስቱ› ማለትም፡ ኪዳነ አዳም ወሔዋን፥ ኪዳነ ኖኅና ኪዳነ መልከ ጼዴቅ፡ በቀጥታ፡ ተወርሰው፥ ተጠብቀውና ጸንተው የኖሩት፡ በኢትዮጵያ ልጆች ሲኾን፡ የኋለኞቹና ተከታታዮቹ ሦስቱ ደግሞ፡ ማለትም፡ ኪዳነ አብርሃም፥ ኪዳነ ሙሴና ኪዳነ ዳዊት፡ በቀጥታ፡ ለእስራኤል ልጆች ብቻ የተሰጡ ነበሩ።

ነገር ግን፡ ከላይ በሠፈረው ሓተታ፡ በሚበቃ እንደተብራራው፡ እኒሁ፡ የእስራኤል ልጆች፡ የእነርሱ ለኾኑት፡ ለሦስቱም ቃል ኪዳናት፡ ለባለቤትነት ቀርቶ፤ ለባለአደራነት እንኳ ያልበቁ፥ እንዲያውም፡ እነርሱ ራሳቸው፡ የእነዚሁ ቃል ኪዳናት ተቃዋሚዎቻቸውና አፍራሾቻቸው ኾነው መገኘታቸው፡ ባልተቋረጠው ክፉ አድራጎታቸው ከተረጋገጠባቸው፡ በእጅጉ ቆይቷል። ለዚህም፡ ይኸው፡ በአኹኑ ጊዜ እንኳ፡ የቃል ኪዳኖቹ ዋናዎቹና አማናዊዎቹ ምልክቶች፡ በእነርሱ ዘንድ፡ ጨርሰው አለመኖራቸው፡ በገሃድ ለሚታየው እውነታ፡ ተጨማሪ ምስክር ነው።

አዎን! እነዚህ፡ ሦስቱም ቃል ኪዳናት፡ በሙሉ፡ በኪዳናውያቱ የኢትዮጵያ ሴቶች ልጆች፡ በኬጡራና በማክዳ ንግሥት አማካይነት፡ ወደኢትዮጵያ ልጆች እንዲዛወሩ ተደረገ። ኢትዮጵያውያኑና ኢትዮጵያውያቱም፡ በባለደራነት ብቻ ሳይኾን፡ በባለቤትነት ጭምር ተረክበዋቸው፡ በእውነተኛው ሃይማኖትና መንፈሳዊ ምግባር ፈጣሪያቸውን ሲያመልኩባቸው ቆዩ።

የመጨረሻው የምሕረትና የሕይወት ዘመነ ሥጋዌም፡ የተስፋ ቃሉንና ጊዜውን ጠብቆ ሲደርስ፡ ስድስቱ የቀደሙት ቃል ኪዳናት ምሳሌዎቻቸውና አርአያዎቻቸው የኾኑት፡ አማናዊውና ዘለዓለማዊው ሕያው ቃል ኪዳን፡ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አማናዊቷና ዘለዓለማዊቷ ሕያውት ቃል ኪዳን ከኾነችው፡ ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም በኢትዮጵያዊነት ተወለደ። የቀደሙትን ስድስቱን ቃል ኪዳናት በማጠቃለልም፡ ፍጹሙ የአምላክ ቁጥር በኾነው ሰባተኛነት፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ በመለኮታዊው የትስብእት ደሙ ዐተመ።

በዚህ መሠረት፡ እውነተኛው እስራኤላዊነት፡ ለኢትዮጵያ ልጆች ተጨምሮላቸው፡ እስራኤላዊነት፡ በፍጹም የንስሓና የተዋሕዶ ምሥጢራት ጠርቶና ነጽቶ፥ ታድሶና ተቀድሶ፡ ከኢትዮጵያዊነት ጋር አንድ በመኾን፡ በሕያውነት እንዲኖር ተደረገ።

እንዲህ ኾኖ የኖረውና የሚኖረው ኢትዮጵያዊነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፥ ለዘለዓለማዊነት በቅቶ፡ እነሆ፡ በህልውናው ቀጠለ! ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና።